# ሰላዮችን ለማጋላጥ..... ስለሚለው

የግል አስተያየት፣ ከብስራት ኢብሳ         28-10-2011

ሃገርን የሚጎዳ ስራ የሚሰሩ ሰላዮችን ማጋለጥ የእያንዳንዱ ሃገሩን የሚወድ ዜጋ ሃላፊነትም ፣ ግዴታም ስለሆነ ለመደገፉ ምንም ጥርጥር የለውም ፡፡ ነገር ግን የግል ችግርን ለመሸፈን ብቻ ፣ በፖለቲካ ሽፋን ስር ተጠልሎ ግለሰቦችን ለማጥቃት ፣ ፖለቲካን ያለአግባብ መጠቀም ከስለላ ያላነሰ ወንጀል ነው፡፡

ሰላዮችን በማጋለጥ ስም የቂም በቀል ዘመቻ ........የሚለውን ጽሁፍ ሳነብ ፣ አቶ አገሬ ምን ሊሰማዎት እንደሚችል ከጥቂት ወራት በፊት ተመሳሳይ የስም ማጥፋት በሌለ ሰው ስም እኔም ላይ በትነው ስለነበር ስሜቱ ይገባኛል ፡፡ ሳያስቡት የተጋለጡበት ፣ ወረቀቱን ሲበትኑት የእስፖርት አዘጋጁን ሎጎ ይዞ ነው የወጣው፡፡ የእስፖርት አዘጁ በሙሉ እንደዚህ አይነት ወራዳ ስራ ይሰራል የሚል እምነት ባይኖራኝም ፣ ለበጎ ተግባር እንዲገለገሉበት የተባበራቸው የኢትዮጵያ ማህበርም ሆነ ፣ ሌሎቹ የእስፖርቱ ኮሚቴዎች በእስፖርት አዘጋጁ ሎጎ ፣ በ ዋሌ ተመስገን ፣ በፈጠራ ስም መጻፉን ተቃውመው ማንም ማስተባበያ የሰጠ የለም፡፡

እንደገናም ምናልባት እንኳን በስህተት ከሆነ ፣ በእስፖርት አዘጋጁ ስም ይቅርታ እስካሁን የጠየቀ የለም ፡፡እንዲያውም አሁን እንደማነበው ፣ አቶ ሃገሬ በቅርቡ ተደርጎ በነበረው የኦዲት ስብሰባ ሃሳባቸውን ስላቀረቡ ፣ በጥቂት ቀናት ውስጥ እንደዚህ አይነት የተቀነባበረ የስም ማጥፋት ስራ ያውም በሙስና የተዘፈቀ ስርአትን እንቃወማለን ከሚሉ ወገን መሆኑ በጣም አሳዛኝ ነው ፡፡

የኦዲቱን ሪፖርቱን በተመለከተ እራሳቸው በበተኑት ፣ ኦዲተሮች ባሰራጬትም ሆነ በሌሎች በቂ የማቴርያልና የሰዎች ማስረጃ ስህተት ለመሰራቱ ፣ ይህንን አፍጥጦ የወጣን እውነት ለመደበቅ መሞከርና ፣ በዚህም ካፈርኩኝ አይመልሰኝ ፣ እውነቱ እንዲወጣ የሚታገሉትን ሰዎች ፣ እስከዛሬ ተናግረው የማያውቁትን ዛሬ የግል ችግርን ከፖለቲካ ጋር አዛምዶ በዛ ውስጥ ለመደበቅና ፣ እግረ መንገድም አጀብ ለማብዛት መሞከር ፣ እንደኔ ዝሆን ሰርቆ ለመደበቅ መሞከር ነው ፡፡

ምናልባት ኦዲተሮቹም እንደዚህ አይነት ወከባ ፈርተው ከሆነ ፣ ከተመረጡበት የኦዲት ስራ ይልቅ ወደ ሽምግልናው ያመዘኑት፡፡ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ በትክክል ከሚመለከታቸው ሰዎች ይልቅ ፣ በቀጥታ ከገንዘብ ጋር ሃላፊነት የማይመለካታቸውን ሰዎች ስም ጠቅሰው ፣ በሌላ መንገድ ፣ ባከኖዋል ለሚሉት ገንዘብ እንኳን በቀጥታ ፣ በማን ወጪ ሆኖ እንደባከነ ፣ ወይም ፣ ማን ያላስረከበው ገንዘብ በቀጥታ እንደሚመለከተው ፣ ስንት ገንዘብ እንደቀረ ፥ ማን ዘንድ ፣ የመሳሰሉትን በግልጽ ለማስቀመጥ የፈሩ ፣ ወይም ተጸእኖ ያለባቸው ይመስላል፡፡

ያልተመረጡት ኤዲተር አቶ ሃገሬ የተሻለ ሞክረውታል ፡፡ ለምሳሌ  እሳቸው እንዳሉት ለ3 ቀን 15% እንተወውና  ለወር እንኩዋን አበደሩ ብንለው 15% ጊዜ 12 ወር ባመት 180%  ወለድ ከፍለዋል ማለት ነው ፡፡ ይህ በባንክ ዓለም ወለድ አሰጣጥ ጌኒስ መጽሃፍ ውስጥ የሚያስመዘግብ ፣ ጉዳይ አይነቶቹን እንኳን ብዙ መነካካት ስላልፈለጉ ፣ የጥቂቶችን ተጠያቂነት በብዙሁኑ በዓል አዘጋጅ አባላት ውስጥ ማስጠለል የወሰኑ ይመስላል ፡፡

ማንም እስከ ሰራ ይሳሳታል ፡፡ ብዙዎቻችን እውነቱ እንዲወጣ ይህን ግፊት ያደረግነው ሰዎች ሲሰቃዩ ለማየት ፈልገን፣ ወይም የግለሰቦችን ሞራል ለመንካት ሳይሆን ፣ ቢያንስ ከዚህ ተምረን ለወደፊት እንደዚህ አይነት ሃላፊነት የሚወስዱት ሰዎች ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደግሙ  ለማህበረሰባችን ትምህርት ለመስጠት እንጂ ለመጉዳት ቢሆን አቤቱታ የምናሰማው እዛ አልነበረም ፡፡ በጣም ትንሹ ፣ ምንም ዋጋ የማያስከፍለው ሦስት ቃል ፥ ይቅርታ ፣ ካለማወቅ ፣ ይህ ይመጣል፣ ብለን ስላልተዘጋጀን ፣ ከልምድ እጥረት ፣ ሳላውቅ አጠፋሁት ........ወዘተ በራስ ወገን መሃል ይቅርታ ጥይቆ መገላገል እያለ ፣ ስህተትን በስህተት ለመሸፈን መሞከር ቦኋላ ዋጋው ከባድ ነው ፡፡

አንድ ማህበር ፣ አንድ የአመለካከት ሰፈር ውስጥ ስላለን ፣ ከዚህ የሚከብድ ብዙ የምንሰራቸው ጉዳዮች ስላሉ ፥ ሁሉንም ነገር ከዛ ውስጥ ለመጨረስ እንጂ ፣ እንደ ሆላንድ ነጻ ሃገር ያውም በቂ ማስረጃ ኖሮ ፣ እንኳን ጥቂት ሰዎችን ፣ ካጠፉ መንግስትን መክሰስ የምቻልበት ሃገር ነን ፡፡ እንደ ሃገራችን ትንሽ አጀብ ይዞ በግርግር መደበቅ የሚቻልበት ሃገር አይደለንም ያለነው ፡፡ ነገሮች አንዴ ከመስመራቸው ከወጡ መልሶ ማስተካከል ከበድ ነውና ፣ እንደዚህ አይነት የተንኮል ስራ ባስቸኳይ ካልቆመ ፥ ጅብ በቀደደው ዉሻ እንዳይገባ ብለን ነሩን ለማብረድ የምንሞክረውን ፣ ስንት የሃገር ጉዳይ እያለ ፣ እንደተባለው አላስፈላጊ ቦታ እየገፋችሁን ነው ፡፡ ዝም ማለትን እንደ ፍርሃት ወይም የዋህነት የሚያዩ በራሳቸው መንገድ ላይ መሰናከል እያዘጋጁ መሆኑን ተረድተው  ምክር ቢሰሙ ይበጃልና ጊዜያችንን ከዚህ በላይ ባታባክኑብንና እዚህ ላይ ይተሻለ መቋጫ ብታደርጉ ለናንተም ፣ ይህንን እየሰማ ለሚያዝነውም የተሻለ ነው ብዬ የመጨረሻ ምክሬን አስተላልፋለሁኝ፡፡

እውነት መራራ ብትመስልም  ፣ ጣፋጭ ፍሬዋ አያምልጠን፡፡